# ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ዳሰሳ ሪፖርት



**የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ)**
**2014 ዓ/ም**

# ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ዳሰሳ ሪፖርት

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ)
2014 ዓ/ም

# ማውጫ


አሕፅሮተ-ቃላት....ii

መግቢያ....1

ክፍል አንድ....3

አጠቃላይ የዳሰሳው ይዘት....3

1. አላማ....3
2. አስፈላጊት....3
3. ወሰን....3
4. በዳሰሳው የተሳተፉ አካላት....3
5. የዳሰሳው ዘዴ....4
6. የዳሰሳ ቱሎች....5
7. ታሳቢ መደረግ ያለባቸው....5

ክፍል ሁለት....6

የሀገር አቀፍ ተቋማት ስጋት ዳሰሳ ትንተና....6

8. ዳሰሳ የተደረገባቸው ተቋማት....6
9. የትኩረት መስክ....7
   - 9.1. አመራርና አስተዳደር ገዥ ሰነዶች....8
   - 9.2. ግንዛቤና ባህል ግንባታ....9
   - 9.3. አቅም ግንባታ....10
   - 9.4. አመራርና አስተዳደር ስርአት....11
   - 9.5. መሰረተ-ልማት....12
10. ማጠቃለያ....13

# አሕፅሮተ-ቃላት

| | |
|---|---|
| **ኢመደኤ** | ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር |
| **ISO** | International Organization for Standardization |
| **NIST** | National Institute of Standard and Technology |
| **OWASP** | Open Web Application Security Project |

# መግቢያ

ባለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን የሳይበር ምህዳር መፈጠር አለማችንን ወደ ትንሽ መንደር በመቀየር ዓለም አቀፋዊነት ሉላዊነትን አስከትሏል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ከሳይበር ምህዳር ውጪ መሆን የማይቻልበት፣ ያለ ሳይበር አቅም እንደ ሃገርም ሆነ ተቋም ተወዳዳሪ ሆኖ መዝለቅ ይቅርና ህልውናን ማስጠበቅ የማይቻልበት ደረጃ እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሳይበር ምህዳር ከፍተኛ የደህንነት ስጋት እና አደጋ ያለበት ሆኗል፡፡ ስሆነም ተቋማት ደህንነቱ የተጠበቀ የሳይበር ምህዳር ለመፍጠር ሌት ተቀን መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም በሀገሪቱ ያሉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችና ተቋማት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ጎን ለጎን የሳይበር ደህንነት ተግባራትን ማለትም ሳይበር አሁን ካለበት ደረጃ የሚመጥን የደህንነት ተግባራት ማከናወንና የሚደርስባቸውን ጥቃት ለመከላከል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ትኩረት ሰጥተው ሊተገብሩት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በአሁን ሰአት ሀገራት የሳይበር ምህዳሩ መስፋትና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ማደግ ጋር ተያይዞ የሚገጥማቸው የሳይበር ጥቃት በጣም ከፍተኛ ስለሆነና ይሄን የሚመጥን የደህንነት መቆጣጠሪያ መንገዶች መጠቀም የግድ ሲሆን ቀድሞ የደህንነት መከላከያ ተግባራትና ስትራቴጂዎች መንደፉ አደጋው ከሚያደርሰው የኢኮኖሚ ኪሳራ መቀነስ ያስችላል፡፡ ከኢኮኖሚ እይታ ወይም በኢኮኖሚ ላይ ከሚያሳድረው ተፅእኖ በተጨማሪ በተቋም ከፍ ሲልም በሀገር ደረጃ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ፣ በቴክኖሎጂ፣ በህግ እንዲሁም በካባቢያዊ አንፃር የሚያሳድረው ጫናና ተጽእኖም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

በመሆኑም ቁልፍ መሰረተ ልማቶችና ተቋማት ደህንነታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ከመሆኑም በዘለለ የቁልፍ መሰረተ-ልማቶችን ደህንነት ማረጋገጥ ለሀገሪቱ የሰላም፣የልማትና የዲሞክራሲያው መርሃ ግብሮች ማስፈፀሚያ እንዲሆኑ ያግዛል፡፡ በመሆኑም ይህ የሳይበር ደህንነት ስጋት ዳሰሳ በሀገሪቱ ያሉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ቁልፍ መሰረተ ልማቶች በሳይበር ምህዳሩ ከሚደርስባቸው ጥቃትና ደህንነትን ከማስጠበቅ አንፃር ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ እንዲሁም ቁልፍ ሀብቶታቸቸውን ከጥቃት ለመከላከል ሊተገብሩ የሚገባቸውን ተግባራትና ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች የሚያስፈልጓቸውን በሚያሳይ መልኩ ያስቀመጠ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተቋማቱ ሀብቶች ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶች የሚያደርሱት ተጨባጭ ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚካዊ፣ ማህበራዊ ተፅእኖ መተንተን እና የመቆጣጠሪያ አማራጮች ማየትን ያካትታል፡፡ በተቃራኒው ቁልፍ ተቋማት ሀብቶቻቸው ደህንነታቸው ካልተረጋገጠ ከኃይልና ሃብትነታቸው ይልቅ ለልማት ማደናቀፊያነትና ለጸረ-ዲሞክራሲያዊ ተግባር የመዋል እድላቸው ሰፊ ነው፡፡

የሳይበር ደህንነት ዳሰሳ ሪፖርቱ ለማዘጋጀት በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ተቋማት ላይ ዳሰሳ በማድረግ፣በተለያዩ በተቋማቱ ላይ የፍተሻና ቁጥጥር ስራዎችን በመስራት ያሉ ክፍተቶችን በመለየትና እንዲሁም በቁልፍ ተቋማቱ ላይ በየጊዜው የሚያጋጥሙ የሳይበር ጥቃቶችን ዳታ አናላይዝ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን የዳሰሳ ዶክመንቱ በዋናነት

በየተቋማቱ ያሉ አጠቃላይ ጥንካሬዎች፣ ክፍተቶች ምቹ ሁኔታዎችንና ተግዳሮቶችን እንዲሁም የተቋማቱ ሀብቶች ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶች፣ የሚያደርሱት ተጨባጭ ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚካዊ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂ፣ ህጋዊ እና ከባቢያዊ ተፅእኖ በሚያሳይ መልኩ የተዘጋጀ ነው ፡፡

# ክፍል-አንድ

## አጠቃላይ የዳሰሳው ይዘት

### 1. አላማ

የዚህ የስጋት ዳሰሳ ዋና አላማ በሀገሪቱ ያሉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችና ተቋማት ሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲችሉ ያሉበትን አቋም የማየትና የሳይበር ደህንነት ተግባራትን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ እንዲተገብሩ ማሳያ ነው፡፡

### ዝርዝር አላማዎች ፡-

- ሀገራችን በሳይበር ደህንነት ላይ ያለችበትን ቁመና ማሳየት፣
- ምርምርና ጥናት ለሚሰሩ አካላት ግብአት እንዲሆን፣
- ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ እስትራቴጂ፣ ፖሊሲ እና ሌሎች ማእቀፎች ለሚያዘጋጁ አካላት ግብአት ለማዘጋጀት
-

### 2. አስፈላጊነት

የሳይበር ደህንነት ስጋት አስተዳደር ዳሰሳ የሳይበር ምህዳሩ በየወቅቱ ተቀያያሪና ተለዋዋጭ በመሆኑና የሀገሪቷ ቁልፍ መሰረት ልማቶችና ተቋማትን ከሳይበሩ ከሚጠይቀው አቅም ጋር አብረው መጓዝ እንዲያስችላቸው አሁን ያሉበትን አቋም በማሳየት ተቋማት የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራቶችን ቀድመው እንዲያከናውኑ ይረዳቸዋል ፡፡

### 3. ወሰን

ይህ ሰነድ የሚዳስሰው በተቋማቱ ስትራቴጂካዊና ታክቲካል የሳይበር ደህንነት ዳሰሳ ሲሆን ኦፕሬሽናል ስጋት ዳሰሳ በተወሰነ መልኩ ተካቷል፡፡


### 4. በዳሰሳው ተሳታፊ አካላት

በተካሄደው የስጋት ዳሰሳ ወቅት ከቁልፍ መሰረተ ልማትና ተቋማት ወይም ሚኒስቴር መ/ቤቶችን ያካተተ ሲሆን በዚህም በአብዛኛው በየሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሉ ከፍተኛ አመራሮች በስጋት ዳሰሳው ወቅት የተሳተፉ ሲሆን ከነዚህም ሚንስቴሮች፣ ሚኒስቴር ዴኤታዎች፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊ እንዲሁም የእያንዳንዱ ተቋም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክፍል ዋና ኃላፊዎች ተሳትፈዋል፡፡

## 5. የዳሰሳው ዘዴ

በሳይበር ደህንነት ስጋት ዳሰሳ ወቅት መረጃ ወይም የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ይዞታ ምን እንደሚመስል መረጃ የሰበሰብንበት ዘዴ የሚመለከታቸውን የበላይ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማድረግ፣ የተለያዩ በተቋሙ ውስጥ ያሉ ፖሊሲዎች ፣ የአሰራር ሂደቶችና ለስጋት ዳሰሳ የሚያግዙ ዶክመንቶች የተዳሰሱ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በተወሰኑ ሚኒስቴር መ/ቤት የመስክ ጉብኝት /site-visit/ ተደርጓል፡፡

- **ቃለ- መጠይቅ፡** በዚህ ዘዴ ዳሰሳ ለማድረግ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በተቋማቱ ውስጥ ከሚገኙ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በሚደረግ የገጽ ለገጽ ውይይት መረጃዎችን የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል።
- **የጽሑፍ መጠይቅ፡** በዚህ የዳሰሳ ዘዴ በተቋማቱ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ሰራተኞች የሚሞሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል።
- **የመስክ ምልከታ፡** በዚህ የዳሰሳ ዘዴ በተቋማቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ሀብቶችን የመስክ ምልከታ በማድረግ መረጃዎችን የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል።




ምስል 1 የዳሰሳ ዘዴ

## 6. የዳሰሳ ቱሎች

የሳይበር ደህንነት ዳሰሳ ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚረዱ በሀገር ውስጥ የተዘጋጁ እንዲሁም አለም አቀፍ ቱሎችን ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በዋናነት እነዚህን ቱሎች የተመረጡት በስትራቴጂክ፣ ታክቲካልና ኦፕሬሽናል ደረጃ ዳሰሳ በማድረግ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እና የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር ነው።

**ጥቅም ላይ የዋሉ ቱሎች**

| ተ.ቁ | ቱሎች |
|---|---|
| 1 | Critical mass cyber security requirement standard |
| 2 | NIST framework |
| 3 | ISO |
| 4 | OWASP |
| 5 | NIST... |

## 7. ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች

በሀገር ደረጃ የሳይበር ደህንነት ሪፖርት በተደራጀ መልኩ ተዘጋጅቶ አያውቅም ይህ ሪፖርት በሀገር ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀ ሲሆን ሪፖርቱን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ መረጃዎች ከ2012-2013 ዓ.ም ባለ ጊዜ ውስጥ የተሰበሰቡ መሆናቸው መረጃዎቹ ከተሰበሰቡበት ጊዜ በኋላ በተቋማቱ ውስጥ የሚኖሩ ለውጦችን በሪፖርቱ ያልተካተቱ መሆናቸው ታሳቢ መደረግ ይኖርባቸዋል።

# ክፍል- ሁለት

## የሀገር አቀፍ ተቋማት ስጋት ዳሰሳ ትንተና

### 8. ዳሰሳ የተደረገባቸው ተቋማት

በዚህ የዳሰሳ የተለያዩ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ተቋማትን በሴክተር ደረጃ በመለየት በሀገር ላይ ያላቸውን ሁለንተናዊ ተጽህኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተለይተው እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡




ምስል 2፡ የተቋማት ዝርዝር መግለጫ

# 9. ሪፖርቱ የተዘጋጀባቸው ይዘቶች/የትኩረት መስክ

የሀገራችንን የሳይበር ደህንነት ቁመና በሚፈለገው ልክ ማሳየት እንዲችል ለማድረግ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች በስትራቴጂክ፣ ታክቲካል እና ኦፕሬሽናል ደረጃ በተሰሩ የዳሰሳ ስራዎች የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የተዋቀረ ሀገራዊ የሳይበር ደህንት ዳሰሳ ሪፖርት ነው።

ይህ ሀገራዊ የሳይበር ደህንት ዳሰሳ ሪፖርት በአምስት የትኩረት መስኮች ተለይቶ በየዘርፉ ያሉ የሳይበር ደህንነት ቁመና ምን እንደሚመስል ተቃኝቷል ፡፡



ምስል 3፡ የትኩረት መስክ

## 9.1 ከአመራርና አስተዳደር ገዢ ሰነዶች አንጻር

የዳሰሳው ውጤት እንደሚያሳየው በሀገራችን ውስጥ የሳይበር ደህንነት ስራዎችን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ገዢ ሰነዶች(ስትራቴጂ፣ ፖሊሲና ሌሎች ማዕቀፎች) በተሟላ መልኩ አልተዘጋጁም፣ የተዘጋጁትም ቢሆኑ እየተተገበሩ ባለመሆናቸው በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ተቋማት የመረጃዎቻቸውን ደህንነት የማስጠበቅ ስራን ወጥ በሆነ መልኩ ለመምራት አስቸጋሪ ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰነዶች በአግባቡ ካልተዘጋጁና ካልተተገበሩ የመረጃዎቹን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚሰሩ ስራዎችን ወጥነት ባለው መንገድ መምራት ስለማይቻል መረጃዎቹ ለጥቃት ተጋላጭ እንዲሆኑ እያደረጋቸው ይገኛል።

**1** | **0-50%**

**ያልበለጸገ ፡- የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች ተያያዥ ማእቀፎች ያልበለፀጉ የምንለው በዋናነት**

- የሳይበር ደህንነትን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ገዢ ሰነዶች(እስትራቴጂ፤ ፖሊሲ እና ሌሎች ገዢ ሰነዶች) አለመኖራቸው፤

**2** | **50-75%**


**በተወሰነ ደረጃ የበለፀገ ፡- የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች ተያያዥ ማእቀፎች በተወሰነ ደረጃ የበለፀጉ የምንለው በዋናነት**

- የሳይበር ደህንነትን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ገዢ ሰነዶች(እስትራቴጂ፤ ፖሊሲ እና ሌሎች ገዢ ሰነዶች) ቢኖሩም እየተተገበሩ አለመሆናቸው እና የትግበራ ሂደቱንም የሚከታተል አካል አለመኖሩ፤

**3** | **ከ 75% በላይ**

**የበለፀገ ፡- የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች ተያያዥ ማእቀፎች የበለፀጉ የምንለው በዋናነት**


- የሳይበር ደህንነትን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ገዢ ሰነዶች(እስትራቴጂ፤ ፖሊሲ እና ሌሎች ገዢ ሰነዶች) መኖራቸውና በቀጣይነት እየተተገበሩ መሆናቸው እንዲሁም የትግበራ ሂደቱንም በትኩረት የሚከታተል አካል መኖሩ፤





ምስል 4፡ አመራርና አስተዳደር ገዢ ሰነዶች

## 9.2 ከግንዛቤና ባህል ግንባታ አንጻር

በዳሰሳው ለማየት እንደተቻለው በሀገራችን በሳይበር ደህንነት ላይ ያለው ግንዛቤና ባህል በጣም አነስተኛ የሚባል ሲሆን ዳሰሳ የተደረገባቸው በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ተቋማት ከከፍተኛ አመራር ጀምሮ እስከ ታችኛው ባለሙያ ድረስ በሳይበር ደህንነት ላይ ያላቸው ግንዛቤ የመረጃዎቹን ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር አነስተኛ በሚባል ደረጃ ላይ ይቀመጣል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የመረጃዎቹን ደህንነት ለማስጠበቅ ምንም አይነት የተራቀቀ የሳይበር ጥቃት መከላከያዎችን መግዛትና መጠቀም ቢቻልም የመረጃዎቹን ደህንነት የማስጠበቅ ስራዎችን የሚሰሩት ሰራተኞችና ስራዎቹ እንዲሰሩ አስፈላጊውን ሀብት የሚመድቡና አመራር የሚሰጡ አመራሮች ስለሳይበር ደህንነት ያላቸው ግንዛቤና ባህል አነስተኛ ነው። ስለሆነም አሁን ባለው ሁኔታ በሀገሪቱ ቁልፍ ተቋማት ላይ የሳይበር የሚያጋጥሙ የሳይበር ጥቃቶች እየጨመሩ ይገኛሉ።




ምስል 4፡ ግንዛቤና ባህል

## 9.3 ከአቅም ግንባታ አንጻር

በሀገራችን ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ የሚሰሩ የ አቅም ግንባታ ስራዎች በጣም አነስተኛ ናቸው ፡፡ ይህ መሆኑም የመረጃዎችን ደህንነት የማስጠበቅ ስራ የሚሰሩ ባለሙያዎች በሀገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚከሰቱ የሳይበር ጥቃቶችን ቀድሞ ለመከላከልና ከተከሰቱም በኋላ በጥልቀት ችግሮቹን በመረዳት መፍትሄ ለመስጠት እንዳቸገሩ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡

**1 — 0-50%**

**ዝቅተኛ**:-የሳይበር ደህንነት የተገነባ አቅም ዝቅተኛ ነው የሚባለው በዋናነት:-

- በመሰረታዊ ደረጃ የሳይበር ደህንነትን ለመምራት የሚያስችል አቅም አለመኖር፤
- በመሰረታዊ ደረጃ ሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ፕሮግራም አለመኖር፤
- ሳይበርን በሚፈለገው መጠን የተረዳ ከፍተኛ አመራር እና ባለሙያ አለመኖር፤
- ለሳይበር ደህንነት የአቅም ግንባታ ስራዎች ለመስራት የሚያስችል በጀት በሚገባ አለመመደቡ

**2 — 50-75%**


**መካከለኛ**:-በተቋማቱ የተገነባ አቅም መካከለኛ ደረጃ ነው የሚባለው በዋናነት :-

- በቂ በሚባል ደረጃም ባይሆን የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ፕሮግራም የተዘጋጀ ቢሆንም በቀጣይነት እየተተገበረ አለመሆኑ
- የሳይበር ደህንነት አቅም ግምባታ ማዕቀፎች የተዘጋጁ ቢሆንም እየተተገበሩ አለመሆኑ እና አተገባበራቸውን የሚከታተል አካል አለመኖሩ፤
- የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ስራዎች ለመስራት ፍላጎት ቢኖርም ስራዎቹን ለመስራት የሚያስችሉ ሀብቶችን በአግባቡ አለማሟላት፤

**3 — ከ 75% በላይ**

**ከፍተኛ**:-የተገነባ አቅም ከፍተኛ ነው የሚባለው በዋናነት

- የአቅም ግንባታ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው እየተተገበሩ መሆኑ እና አተገባበራቸውም በየጊዜው ክትትል የሚደረግበት መሆኑ፤
- የሳይበር ደህንነት አቅም ግንባታ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በቀጣይነት እየተተገበረ መሆኑ
- የሳይበር ደህንነት አቅም ግምባታ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ ሀብቶች በበቂ ሁኔታ መመደባቸው




ምስል 5፡ አቅም ግንባታ

## 9.4 ከአመራርና አስተዳደር ስርአት አንጻር

ዳሰሳው በተደረገባቸው ተቋማት ላይ ለማየት እንደተቻለው በሀገራችን ውስጥ በሚፈለገው ደረጃ የሳይበር ደህንነትን ለመምራት የሚይያስችል የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት የለም፡፡ ይህ መሆኑም የሀገራችንን ቁልፍ መረጃዎችን ደህንነት ለማስጠበቅ መሰራት ያለባቸው ስራዎችን ለማከናወን በአግባቡ የተዋቀረ አደረጃጀት ፤ የተዘረጋ ስርዓቶች በሚፈለገው ደረጃ የሌሉ በመሆናቸው የመረጃዎቹን ደህንነት የማስጠበቅ ስራን ወጥነት ባለው ሁኔታ ለመስራት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

**1** | **0-50%**

**ያልተዘረጋ** :- የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት በተቋማቱ ያልተዘረጋ ወይም ተግባራዊ ያልሆነ ሲባል

- የሳይበር ደህንነትን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት አለመኖሩ፤
- የሳይበር ደህንነት ስራን እንደ ዋናው ስራው የሚሰራ ሳይበር ደህንነት ክፍል በመዋቅራቸው ውስጥ አለመካተቱ፤

**2** | **50-75%**


**በተወሰነ ደረጃ የተዘረጋ** :- የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት በተቋማቱ በተወሰነ ደረጃ የተዘረጋ ወይም ጅምር ላያ ያሉ ከንውኖች ሲባል በዋናነት

- የሳይበር ደህንነትን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት ቢኖርም በበቂ ሁኔታ እየተተገበረ አለመሆኑ፤
- የሳይበር ደህንነት ስራን እንደ ዋናው ስራው የሚሰራ ሳይበር ደህንነት ክፍል ቢዋቀርም በቂ የሰው ሀይልና ሌሎች ሀብቶች አለመመደባቸው፤

**3** | **ከ 75% በላይ**

**የተዘረጋ** :- የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት በተቋማቱ የተዘረጋ ወይም ተዘርግቷል ሲባል በዋናናት


- የሳይበር ደህንነትን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት መኖሩና በበቂ ሁኔታ እየተተገበረ መሆኑ፤
- የሳይበር ደህንነት ስራን እንደ ዋናው ስራው የሚሰራ ሳይበር ደህንነት ክፍል መዋቀርና በቂ የሰው ሀይልና ሌሎች ሀብቶች መመደባቸው፤





ምስል6 ፡ አመራርና አስተዳደር ስርአት

## 9.5 ከመሰረተ ልማት አንጻር

በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ተቋማት የሚገኙ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች የተቋማቱን የአሰራር ስርአት ከማዘመን፣ የሚሰጡዋቸውን አገልግሎቶች ከማቀላጠፍ እንዲሁም ያላቸውን ቁልፍ መረጃዎችን በተደራጀ መልኩ እንዲያዙ በማድረግ ትልቅ ጥቅም አለው ነገር ግን የነዚህን መሰረተ ልማቶች ደህንነት በሚፈለገው ልክ ማስጠበቅ ካልተቻለ መረጃዎቹን ለከፍተኛ ጥቃት ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋል። በአሁኑ ጊዜ የመሰረተልማቶቹን ደህንነት ለማስጠበቅ እየተሰራ ያለው ስራ ከተወሰኑ ተቋማት ውጪ በጣም አነስተኛ ሲሆን እነዚህ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች በከፍተኛ ሁኔታ ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ እንዲሆኑ በር ስለሚከፍት በሀገራችን በአንዳንድ ተቋማት ላይ ሁሉን አቀፍ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል።








ምስል 7፡ መሰረተ ልማት

## 10. ማጠቃለያ

ከዳሰሳው ምልከታ ለማየት እንደተሞከረው የሀገራችን የሳይበር ደህንነት ደረጃ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ሀገራችንን ለከፍተኛ ጉዳት ተጋላጭ እንድትሆን እያደረገ ይገኛል። እነዚህን ችግሮች በፍጥነት መፍታት ካልተቻለ ሀገራችንን ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጉዳት ይዳርጋታል። ስለሆነም በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ተቋማት ያሉዋቸውን ቁልፍ ሀብቶች ደህንነት የማስጠበቅ ስራን ማለትም የወሳኝ አቅም ሳይበር ደህንነት ስታንዳርድን (critical mass cyber security requirement standard) ተግባራዊ ማድረግ፣ የሳይበር ደህንነት ስትራቴጂ እና ፖሊሲዎችን መንደፍ እና መተግበር፣ አናሎግ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ዲጂታል እና ዘመናዊ መቀየር፣ የተለያዩ የሚሰሩባቸው ያሉ ፕሮሲጀሮችን ዶክመንት ማድረግ እና ተግባራዊ ማድረግ፣ የተለያዩ የሳይበር ስጋት አስተዳደር፣ የአደጋ መልሶ ማገገሚያ እና የስራ ቀጣይነት ፕሮግራሞችን መቅረጽ እና መተግበር፣ የሳይበር ደህንነት የስራ ክፍሎችን ከዋናው አደረጃጀት ጋር በማይፃረር መንገድ በማቋቋም ተግባራዊ ማድረግ ፣ በተፈጠረውም አደረጃጀት ላይ አስፈላጊውን እና ብቁ የሆነ የሰው ሀይል በመመደብ ስራዎችን መስራት፣ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ቴክኖሎጂዎች ዘመኑ ባፈራቸው ቴክኖሎጂዎች መቀየር የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ስራ የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

የሀገሪቱን የሳይበር ደህንነትን የማስጠበቅ ሀላፊነትና ስልጣን ያለው የመንግስት አካልም (ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር) በሀገር ደረጃ የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ገዢ ሰነዶችን (ስትራቴጂ፣ፖሊሲ ሌሎች ማዕቀፎች) በማዘጋጀት እንዲሁም የተዘጋጁትንም እንዲተገበሩ አስገዳጅ ህጎችን በማውጣት ፣ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ስርአት፣ በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ለማብቃት የሚያስችል የሰው ሀይልና የመረጃዎችን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል የቴክኖሎጂ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በሚፈለገው ልክ በቀጣይነት ለመስራት የሚያስችል ተግባሮችን እንዲያከናውኑ ማድረግ፣ በሀገር ደረጃ የሳይበር ደህንነት ላይ ግንዛቤና ባህል ለማስጨበጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ሳይበር ደህንነት የአተገባበር ሂደቱን በቅርበት የማረጋገጥ ስራ መስራት ይኖርበታል።


ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት የስጋት ዳሰሳ ሪፖርት
3406
2898
1087
791
706
468
188
1142
542
403
853
657
964
887
2014
2013
2012
2011

+251-11-371-71-14
Fax: +251-11-3-20-40-37
P.O.BOX: 124498
contact@insa.gov.et
www.facebook.com/INSA.ETHIOPIA
www.insa.gov.et
Addis Ababa
Ethiopia